በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ያን ማኅበረ ቅዱሳን አዲስ አበባ ማዕከሌ ት/ሐ/አ/ክፍል ሥርዓተ ት/ት
ንዑስ ክፍል የትምህርት ዓይነቶች ምንነት፣ ዓላማና ይዘት
ነገረ ቅዱሳን (ነገቅ 323) (10 ሰዓት)

<u>የትምህርቱ ምንነት</u>፡-

መግቢያ፡- ልዑለ ባሕርይ አምላካችን እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ብሎ መመሪያ ያስቀመጠልን ቅዱሳንና ያለነውር እንሆን ዘንድ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ሰጥቶን ነው፡፡ ይህም ማለት ሃጢአትን ድል የምንነሳበትንና ወደ ቅድስና ልንደርስ የምንችልበትን ጸጋ ከመስጠቱም በላይ በመንፈስ ቅዱስ ልጅነት አክብሮ አባ አባ ብለን የምንጣራበትን ሥልጣን አድሎናል፡፡ ይህንን የተሰጣቸውን የልጅነት መንፈስና ሥልጣን በአግባቡ ተጠቅመው በጸጋ ላይ ጸጋ ተጨምሮላቸው የተጠሩበት የቅድስና ክብር ላይ ስለደረሱ አበውና እመው ማወቅና መረዳት ለአንድ ክርስትያን እርሱም የተጠራበትን ክብር እንዲረዳና እንዲያስታውስ ከማድረጉም በላይ በሃጢአት እንዳይሸነፍና እንዳይወድቅ ድጋፍ ይሆነዋል፡፡ ከዚህ በላይ ክርስትና በአጸደ ነፍስና በአጸደ ሥጋ ያሉ በመንፈስ የሚገናኙበት የኅብረትና የተስፋ ኑሮ ስለሆነ እነዚህ ቅዱሳን የተሰጣቸውን ክብር አውቆ ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት በተሰጣቸውም ጸጋ መጠቀም እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ የነገረ ቅዱሳን ትምህርት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ከትምህርተ ሃይማኖት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ከሥርዓተ ቤተክርስትያን ትምህርት ቀጥሎ እንዲማሩት ተደርጎዋል፡፡

<u>የትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች</u>:- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ
ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋሊ፡-

- የቅድስናን ምንነት ዓላማና ግብ ይረዳሉ።
- በቤተክርትያን አስተምሕሮ የነገረ ቅዱሳን ትምህርት አስፈላጊነት ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ።
- የቅዱሳን አሰያየም እና መዓረጋተ ቅድስና።
- የቅድስና መገለጫ እና ስለተጋድሎ ይገነዘባሉ።
- ቅዱሳን በክርስትና ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ቦታ ይገነዘባሉ።
- የቅዱሳንን ቃልኪዳን አማላጅነትና ትራዳኢነት ያብራራሉ።
- ስለቅዱሳን መታሰቢያ ምንነት እና አስፈላጊነት ከቅዱስ መጽሐፍ አንጻር።
- ለቅዱሳን የሚገባ ምስጋና ምንነትና አስተምህሮ ያብራራሉ።

ምዕራፍ አንድ:- የነገረ ቅዱሳን ትምህርት መሰረታውያን (2 ሰዓት)

1.1 ቤተክርስትያን የሰማያውያን እና የምድራውያን ሕብረት
1.2 ቅድስና እና የቅድስና ባሕርያት
1.3 የቅድስና ዓላማ እና ግቡ
1.4 የነገረ ቅዱሳን ትምህርት ጽንሰ ሀሳብ
1.5 የነገረ ቅዱሳን ትምህርት አስፈላጊነት

ምዕራፍ ሁለት :- ቅዱሳን እነማን ናቸው (2 ሰዓት)

2.1 ቅዱሳን ሰዎች
- 2.1.1 የቅድስና መገለጫ
- 2.1.2 የቅዱሳን ክብር እግዚአብሔርን እስከመምሰል
- 2.1.3 የቅዱሳን የተጋድሎ ህይወት (ከውስጥ እና ከውጪ)
- 2.1.4 የቅዱሳን አሰያየም (cannonization of saints)
- 2.1.5 መዓረጋተ ቅድስና
  - ንጽሀ ስጋ
  - ንጽሀ ነፍስ
  - ንጽሀ ልቡና

2.2 ቅዱሳን መላእክት
- 2.2.1 የቅዱሳን መላእክት አፈጣጠርና አገልግሎት
- 2.2.2 የቅዱሳን መላእክት ባህርያት
- 2.2.3 ቅዱሳን መላእክት እና ክርስትና

ምዕራፍ ሶስት :- ክብረ ቅዱሳን (3 ሰዓት)

3.1 ቃል ኪዳን፣አማላጅነትና፣ ተራዳኢነት
3.2 መታሰቢያ (ዝክር)
3.3 ምስጋና